UNHCR
The UN Refugee Agency

# ጥገኝነት በአየርላንድ:-

## ለወጣቶች የሚሆን መመሪያ



# ጠቃሚ የግል መረጃ

ስም፡- ..........................................................................................................

የግንኙነት መረጃዎች፡- ..........................................................................................

የጥገኝነት ማመልከቻ ማጣቀሻ ቁጥር:- ......................................................................

የተስላ ማህበራዊ ባለሙያ ስም እና የግንኙነት መረጃዎች፡- ..............................................

..........................................................................................................................

የጠበቃ ስም እና የግንኙነት መረጃዎች፡- ....................................................................

..........................................................................................................................

የ PPS ቁጥር:- ...................................................................................................

የግል ማስታወሻዎች:- ...........................................................................................

..........................................................................................................................

..........................................................................................................................

..........................................................................................................................

..........................................................................................................................

# ይዘት




1. ስለ መመሪያው ........ 7
2. ለጥገኝነት ማመልከት ማለት ምን ማለት ነው? ........ 9
3. ለጥገኝነት ከማመልከትዎ በፊት ........ 15
4. በአየርላንድ ውስጥ የጥገኝነት ማመልከቻ ሂደት ........ 19
5. የዓለም አቀፍ ጥበቃ ቢሮ ሂደት ........ 23
6. የዓለም አቀፍ ጥበቃ ቢሮ ውሳኔ ........ 33
7. የዓለም አቀፍ ጥበቃ ይግባኞች ጉባዔ ........ 35
8. ሌላ መረጃ ........ 43
9. የእርስዎ መብቶች ........ 47
10 ሌሎች ድርጅቶች ........ 51

# 1.

# ስለ መመሪያው

# ይህ መመሪያ በአየርላንድ ውስጥ ጥገኝነት ለሚጠይቁ ከወላጆቻቸው ጋር ያልሆኑ ልጆች እና ለወጣቶች የተዘጋጀ ነው።

በጥገኝነት አሰራር ሂደት ውስጥ ያሉትን የተለያዩ ደረጃዎች ያብራራል።[1] የተወሰኑ ቃላቶች በጥገኝነት አሰራር ሂደት ውስጥ የተለዩ ትርጉሞች ይኖራቸዋል ስለዚህ " ከወላጆቻቸው ጋር ያልሆኑ ልጆች" የሚለውን ቃል አስቀድመን እንመልከት። **ከወላጆቻቸው ጋር ያልሆኑ ልጆች ማለት ከወላጆቻቸው ወይም እንክብካቤ እና ጥበቃ ሊያደርጉላቸው በሚችሉ ሌሎች ማናቸውም ግለሰቦች ለምሳሌ እንደ ሞግዚት ያሉ ኃላፊነት ያለባቸው ሰዎች አብረዋቸው የሌሉ ልጆች ናቸው።**[2]

የጥገኝነት አሰጣጥ የአሰራር ሂደትን በተመለከተ ለበለጠ መረጃ
የእኛን ምስሎች www.unhcr.org ላይ ይመልከቱ።




---

1. ማሳሰቢያ፡- ይህ መመሪያ ለመረጃ ዓላማ ብቻ የተዘጋጀ ሲሆን የሕግ ምክርን የያዘ አይደለም እንዲሁም ሊለወጥ የሚችል ነው።
2. በአየርላንድ ሕግ ልጅ ማለት እድሜው ከ 18 ዓመት በታች የሆነ ሰው ነው። በዚህ መምሪያ ዉስጥ ‘ወጣት ሰው ' የሚል ቃል ስንጠቀም በአሥራዎቹ ዕድሜ ውስጥ የሚገኙ ከ18 ዓመት በታች የሆኑትን ያመለክታል።

# 2.

# ለጥገኝነት ማመልከት ማለት ምን ማለት ነው?

# ለአየርላንድ የጥገኝነት ማመልከቻ ሲያስገቡ፣ ወደ ሀገርዎ ለመመለስ ስለሚፈሩ የአየርላንድ መንግስት ደህንነትዎን እንዲጠብቅልዎ እየጠየቁ ነው ማለት ነው።

'ጥገኝነት' አንዳንድ ጊዜ 'ዓለም አቀፍ ጥበቃ' ይባላል። **የጥገኝነት አሰራር ሂደት ማለት የአየርላንድ መንግስት ወደ አገርዎ ለምን መመለስ እንደማይችሉ እና ለምን በአየርላንድ ጥገኝነት ለማግኘት እንደሚፈልጉ የሚመለከት ነው።**

በአየርላንድ፣ በአገርዎ ውስጥ ውስጥ ጉዳት እንዳይደርስብዎ የሚከላከሉ ሁለት ዓይነት ጥበቃዎች አሉ:-

1. **የስደተኝነት ሁኔታ**
2. **ንዑስ ጥበቃ**

ለጥገኝነት በሚያመለክቱበት ጊዜ የአየርላንድ መንግስት የሚያስፈልግዎ የስደተኛነት ሁኔታ ነው ወይስ የንዑስ ጥበቃ የሚለውን ይመለከታል። በተጨማሪም በአየርላንድ መቆየት ያለብዎ ለምን እንደሆነ የሚያስረዱ ሌሎች ምክንያቶችም ካሉ ይመለከታሉ። ይህም ለመቆየት የተሰጠ ፈቃድ በመባል ይጠራል። በአየርላንድ ውስጥ የዓለም አቀፍ ጥበቃን የሚመለከተው ዋነኛ ሕግ **የዓለም አቀፍ ጥበቃ ሕግ 2015 ነው።**

# ስደተኛ ማነው?

**አንድ ስደተኛ ወደ ሀገር ቤቱ ወይም ቤቷ መመለስ የማይችል ሰው ነው።**
**ይህም በአንድ ወይም ከዚያ በላይ በሚሆኑ**
**ከዚህ በታች በተዘረዘሩ ምክንያቶች የተነሳ ወደ ሃገራቸው ለመመለስ የማይችሉ ከሆነ ነው፤ ለምሳሌ፡-**

- **በፖለቲካ አመለካከታቸው**
- **በሀይማኖታቸው**
- **በዘራቸው**
- **በዜግነታቸው**
- **የ 'አንድ የተወሰነ ማኅበራዊ' ቡድን አባልነታቸው** ፣ በሌላ አባባል አንድ የጋራ የሆነ እና ሊለወጡት የማይችሉት ማንነት ያላቸው ሰዎች ናቸው። በዚህ የጋራ ባህርይ ምክንያት በማኅበረሰባቸው ውስጥ እንደ አንድ ቡድን ይታያሉ እና በውጤቱም አደጋ ላይ ሊወድቁ ይችላሉ። ለተወሰኑ የማህበራዊ ቡድኖች ሊሰጡ የሚችሉ ባህሪያት ምሳሌዎች የሚያጠቃልለዉ ጾታ፣ ፆታዊ ዝንባሌን እና / ወይም አንድ ሰው ቀደም ሲል የተወሰነ ቡድን አባል፣ ለምሳሌ ወታደር ከሆነ ።

እነዚህ ምክንያቶች በቤተሰብዎ አባል የፖለቲካ አመለካከት፣ ሃይማኖት፣ ዘር፣ ዜግነት ወይም የአንድ ማኅበራዊ ቡድን አባልነት ላይ መሰረት በማድረግ ሊሆን ይችላል። ስቃይ ህጋዊ ቃል ሲሆን ህገ-ወጥ ድርጊቶችን፣ ሁከትን ወይም ሌላ ዓይነት ጉዳትን ጨምሮ በርካታ ነገሮችን ሊያካትት ይችላል። የህግ ጠበቃዎ የስቃይን ትርጓሜ ለእርስዎ ሊገልጽልዎ ይችላል።



# ንዑስ ጥበቃ ማለት ምን ማለት ነው?

የስደተኛነት ሁኔታሁኔታ ያልተሰጣቸው ሰዎች ንዑስ ጥበቃ ይደረግላቸው ይሆናል። **የንዑስ ጥበቃ የሚሰጠዉ ወደ ሀገራቸው ቢመለሱ ከባድ አደጋ ይደርስባቸዋል ተብሎ ለሚታሰብ ሰዎች ነዉ።** አንዳንድ የከባድ አደጋ ምሳሌዎች፡-

- **የሞት ቅጣት**
- **ማሰቃየት**
- **ኢሰብአዊ ወይም ክበረ-ነክ አያያዝ**
- **በጦርነት ሳቢያ በህይወትዎ ላይ በሚፈጠር ከባድ ስጋት**

እነዚህ ቃላት ውስብስብ ናቸው ነገር ግን **ጠበቃዎ** እነዚህን ቃላት መግለጽ እና በእርስዎ ማመልከቻ ላይ እንዴት ተግባራዊ ሊሆኑ እንደሚችሉ ሊያብራራልዎ ይችላል።

በአንዳንድ ሁኔታዎች፣ እርስዎ ከአገር ከወጡ በኋላ በአገርዎ ውስጥ በተከሰቱ ምክንያቶች ሳቢያ ስቃይ ወይም ከባድ ጉዳት እንዳይደርስብዎ ሊፈሩ ይችላሉ። ጥገኝነት ለማግኘት በአገርዎ ውስጥ ስቃይ ወይም ከባድ ጉዳት የደረሰብዎ መሆን አይኖርብዎትም። ሆኖም ፣ እርስዎ ወይም የቅርብ ወዳጆችዎ ባለፉት ጊዜያት ስቃይ ወይም ከባድ ጉዳት ከደረሰብዎ በአየርላንድ ጥገኝነት ለማግኘት ያቀረቡት ጥያቄ በሚታይበት ጊዜ፣ ለማህበራዊ ባለሙያባለሙያዎ እና ጠበቃዎ ማሳወቅዎ በጣም አስፈላጊ ነው።

# የመቆየት ፈቃድ ማለት ምን ማለት ነው?

**የመቆየት ፈቃድ የስደተኛነት ሁኔታ ወይም የንዑስ ጥበቃ ፍላጎት ባይኖርዎትም እንኳን በአየርላንድ ውስጥ ለመኖር እና ለመቆየት የሚፈቅድ የስደተኝነት ፈቃድ ነው።** የቤተሰብዎን ወይም ግላዊ ሁኔታዎን ጨምሮ፣ ለመቆየት እንዲፈቀድልዎ ያሚያስችሉ በርካታ ምክንያቶች አሉ። የፍትህና እኩልነት ሚኒስቴር የመቆየት ፈቃድ ለመስጠት ውሳኔለማስተላለፍ የሚከተሉትን ይመለከታሉ:-

- ለምን ያህል ጊዜ በአየርላንድ ውስጥ እንደቆዩ እና ምን ጠቃሚ ግንኙነቶች እንዳለዎት
- ከባድ የሕክምና ምክንያቶችን ጨምሮበሰብአዊነት ምክንያት
- በአየርላንድ እና በሌሎች ሀገሮች ያሳዩትን ባህርይ፣ በወንጀል ጥፋተኛ ሆነው መገኘት አለመገኘትዎን ጨምሮ
- ሌሎች አስፈላጊ ምክንያቶች።

## ለመቆየት ፈቃድ ያቀረቡትን ማመልከቻ ሊያግዝ ይችላል ብለው የሚያስቡት ማንኛውም መረጃ ካለዎት ለማኅበራዊ ባለሙያ እና ለጠበቃዎ ይንገሩ።

**ለምሳሌ ፣ በጥገኝነት አሰራር ሂደት ወቅት የእርስዎ የግል ሁኔታ ሊለወጥ ይችላል፣ የግማሽ ጊዜ ሥራ ሊያገኙ ወይም ተጨማሪ የትምህርት ኮርሶች ሊጨርሱ ይችላሉ፣ ስለዚህ ስለ እነዚህ ለውጦች ማህበራዊ ባለሙያ እና ጠበቃዎ እንዲያውቁ መንገርዎን ያረጋግጡ።**

# በጥገኝነት አሰራር ሂደት ወቅት ያሉኝ መብቶች ምንድናቸው?

በጥገኝነት አሰራር ሂደት ውስጥ አዋቂዎች የሚያገኟቸው መብቶች ሁሉ አሉዎት፤ ነገር ግን የሚከተሉትን ጨምሮ አንዳንድ ተጨማሪ መብቶችም አሉዎት፡-

- **ለእርስዎ የበለጠ ጥቅም የሚሰጠውን የማግኘት መብትዎ ከግምት ውስጥ መግባቱ:** ይህ ማለት እርስዎን የሚመለከቱ ሁሉም ድርጊቶች እና ውሳኔዎች ለእርስዎ የተሻለው ሁኔታ ላይ የተመሠረቱ መሆን አለባቸው ማለት ነው።
- **የመሰማት መብት፡-** ይህ ማለት አዋቂዎች በእርስዎ ላይ ተጽእኖ በሚያሳድሩ ጉዳዮች ላይ ውሳኔ በሚወስኑበት ጊዜ መሆን አለበት ብለው ያሰቡትን ነገር በነጻነት መናገር እና አስተያየትዎም ከግምት ውስጥ መግባት አለበት ማለት ነው።



# 3.

# ለጥገኝነት ከማመልከትዎ በፊት

# ዕድሜዎ ከ 18 ዓመት በታች ከሆነ፣ ከአገርዎ ወጥተው እና ከአየርላንድ ውስጥ ከወላጅዎ ወይም አሳዳጊዎ ተለይተው የሚኖሩ ከሆኑ ብቻውን/ዋን ያለ/ች ልጅነው የሚባሉት።

በአየርላንድ ውስጥ ብቻውን/ብቻዋን ያለ/ች ልጅ እንደመሆንዎ መጠን **ተስላ የተሰኘው የልጆች እና የቤተሰብ ድርጅትተስላ ውስጥ**ከቤተሰብ የተለዩ የስደተኛነት ጠያቂ ልጆች ቡድን ይላካሉ። ይህ ቡድን በአየርላንድ ዕድሜዎ ከ 18 ዓመት በታች በሆኑበት ጊዜ ሁሉ ለእርስዎ እንክብካቤ ኃላፊነት አለበት።



## "በጦርነቱ የተነሳ ከአገሬ ለመውጣት ተገደድኩ።

**በዚህ አስቸጋሪ ጉዞ ላይ ከቤተሰቤ ተለየሁ። አየርላንድ ስደርስ ብቻዬን ነበርኩ"**

ወደ ተሰላ በሚላኩበት ጊዜ በአየርላንድ ውስጥ የጥገኝነት ማመልከቻ መጠየቅ ለርስዎ ይጠቅም አይጠቅምየሚያውቅ **ማህበራዊ ባለሙያ** ይሰጥዎታል።

ማህበራዊ ባለሙያዎ ለጥገኝነት ጥያቄ ማመልከት እንዳለብዎ ከወሰነ፣

## "የማኅበራዊ ጉዳይ ሰራተኛ ነኝ። ወጣቶችን በሁሉም ፍላጎቶቻቸው እረዳለሁ።

እነዚህ ፍላጎቶች የት እንደሚኖሩ እና የት ትምህርት ቤት እንደሚሄዱ እና ከተቻለ ከቤተሰቦቻቸው ጋር መነጋገርን ሊጨምሩ ይችላል። ከእያንዳንዱ ወጣት ጋር በእሱ ወይም በእሷ ፍላጎቶች እና ለእራሳቸው ጥቅም የሚያስፈልጉ የእንክብካቤ እቅዶችን እነድፋልሁ። የዚያ የእንክብካቤ እቅድ አካል በመሆን አንዳንድ ጊዜ ወጣቱ ለጥገኝነት ማመልከት እንዳለበት እንስማማለን። በተለምዶ እንዲህ ዓይነት ውሳኔ ላይ ለመድረስ ከጠበቃ እርዳታ እንቀበላለን"



እሱ / እሷ ከእርስዎ ጋር እንዲሠራ ጠበቃ ለማዘጋጀት **የሕግ እርዳታ ቦርድ** ያነጋግራል። ይህ ጠበቃ ህጋዊ ምክር ያቀርባል እናም በዚህ ሂደቱ ላይ እርስዎን ያግዛል።



**የጠበቃዎ ሚና፡-** ጠበቃዎ የጥገኝነት ማመልከቻዎትን በተመለከተ ይረዳዎታል። እሱ ወይም እሷ በአየርላንድ ለምን ጥገኝነት እንደፈለጉ ለማወቅ ይረዱዎታል። ስለ ሁሉም ፍርሃቶችዎ ለእርሱ ወይም ለእርሷመንገርዎ በጣም አስፈላጊ ነው። ከጠበቃዎ ጋርማንኛውም ዓይነት ችግር ካለብዎት ማህበራዊ ባለሙያዎን ማነጋገር ይችላሉ።

## አስፈላጊ

**የቤተሰብ ፍለጋ፡-** ቤተሰቦችዎ የት እንዳሉ አያውቁ ይሆናል ፣ ነገር ግን የአየርላድ ቀይ መስቀል (የቤተሰብን መልሶ ማገናኘት ተቋም) ቤተሰብዎን እንዲያገኙ ሊረዳዎ ይችላል። ይህ የቤተሰብ ፍለጋ ሂደት በማንኛውም የጥገኝነት ማመልከቻ ሂደት ወይም ቀድሞውኑ ሊከናወን ይችላል። ይህ ለእርስዎ ጥቅም ከሆነ ፣ ተስላ ቤተሰብዎን ለማፈላለግ ይረዳዎታል፤ ይህ የእንክብካቤ ዕቅድዎ አካል ሊሆን ይችላል።

በጥገኝነት ማመልከቻዎ ሂደት ወቅት በሆነ አጋጣሚ ከቤተሰብዎ ጋር ግንኙነት ካደረጉ ማህበራዊ ባለሙያዎ እንዲያውቀው ያድርጉ።

# 4.

# በአየርላንድ ውስጥ የጥገኝነት ማመልከቻ ሂደት

# የጥገኝነት ማመልከቻዎች ላይ ውሳኔዎችን የሚወስነው ማነው?

ጥገኝነት ፈላጊ መሆንዎን የሚመለከቱ በአየርላንድ ውስጥ 2 ቢሮዎች አሉ።

- **የዓለምአቀፍ ጥበቃ ቢሮ**(IPO):- ይህ ጽህፈት ቤት የጥገኝነት ማመልከቻዎን ይመለከታል። የበለጠ ለማወቅ እባክዎ ይህንን ድረ ገጽ ይጎብኙ፡- www.ipo.gov.ie.ie

- **የዓለም አቀፍ ጥበቃ ይግባኞች ጉባዔ** (IPAT)፡- ዓለም የዓለምአቀፍ ጥበቃ ቢሮ (IPO) ጥገኝነት እንደማይገባዎ ከወሰነ ታዲያ በዚያ ውሳኔ ላይ ለዚህ ጉባዔጉባዔ ይግባኝ ማለት ይችላሉ። የበለጠ ለማወቅ እባክዎ ይህንን ድረ ገጽ ይጎብኙ፡- www.protectionappeals.ie



## የጥገኝነት አሠራር አጠቃላይ እይታ:

**1. የጥገኝነት ማመልከቻ**

በመጀመሪያ ወደ ተስላ ይመራሉ። ማህበራዊ ባለሙያው የጥገኝነት ማመልከቻ ማቅረብ ለእርስዎ በጣም የተሻለው አማራጭ እንደሆነ ካመኑ፣ ማመልከቻው ላይ ሊያግዙዎት ይችላሉ። እንዲሁም በዚህ ጊዜ ጠበቃ መጠየቅ ይችላሉ።

↓

**2. አጭር ቃለ መጠይቅ**

ለጥገኝነት ጥያቄዎ ወደዓለምአቀፍ ጥበቃ ቢሮ(IPO) ሲሄዱ አጭር ቃለ መጠይቅ ይኖርዎታል።

↓

**3. መጠይቅ**

የዓለምአቀፍ ጥበቃ ቢሮ (IPO) መጠይቅ ይሰጥዎታል። መጠይቁ ስለእርስዎ መረጃ ይጠይቃል። ማህበራዊ ባለሙያ እና / ወይም ጠበቃዎ በዚህ ረገድ አንዳንድ ምክር ይሰጥዎታል።

↓

**4. ረጅም ቃለ መጠይቅ**

ይህ በዓለምአቀፍ ጥበቃ ቢሮ በጥገኝነት ማመልከቻዎ ላይ ተጨማሪ ጥያቄዎች የሚጠየቁበት ዋና ቃለመጠይቅዎ ነው። የእርስዎ ማህበራዊ ባለሙያ ከእርስዎ ጋር በዚህ ቃለ መጠይቅ ይካፈላል።

**5. ውሳኔ**

ከቃለ መጠይቅ በኋላ የዓለምአቀፍ ጥበቃ ቢሮ (IPO) የጥገኝነት ጥያቄዎ ላይ ይወስናል። የዓለምአቀፍ ጥበቃ ቢሮ (IPO) ጥገኝነት እንደሚያስፈልግዎ ከወሰነ በአየርላንድ ውስጥ እንዲቆዩ ይፈቀድልዎታል፣ እናም የተወሰኑ መብቶች እና ጥቅሞች ይኖሩዎታል። ስለነዚህ መብቶችና ጥቅሞች ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት በዚህ መመሪያ ውስጥ ያለውን ገጽ 47 ይመልከቱ።

**6. ይግባኝ**

የዓለምአቀፍ ጥበቃ ቢሮ፣ ጥገኝነት የማያስፈልግዎ መሆኑን ከወሰነ፣ ማህበራዊ ባለሙያዎ እና / ወይም ጠበቃዎ ውሳኔውን ወደ የዓለም አቀፉ የይግባኞች ጉባዔ አቤቱታ ማቅረብን በተመለከተ ያነጋግሩዎታል።

↓


**7. ይግባኝ ማሰማት**

ይግባኝ ከተጠየቀ፣ የእርስዎ ማህበራዊ ባለሙያ እና ጠበቃ ከእርስዎ ጋር በዓለም አቀፉ የይግባኞች ጉባዔ አቤቱታ የመ(IPO) ስማት ሂደት ላይ መገኘት ይችላሉ።

↓

**8. የዓለም አቀፉ ይግባኞች ጉባዔ (IPAT) ውሳኔ**

ችሎቱ ከተጠናቀቀ በኋላ ፣ የዓለም አቀፉ ይግባኞች ጉባዔ የዓለምአቀፍ ጥበቃ ቢሮ ትክክለ (IPO) ኛውን ውሳኔ የሰጠ እንደሆነ ይወስናል። የዓለም አቀፉ ይግባኞች ጉባዔ ጥገኝነት የሚያስፈልግዎ ሆኖ ካገኘዎት በአየርላንድ ውስጥ ለመቆየት ይፈቀድልዎታል እናምየተወሰኑ መብቶች እና ጥቅሞች ይኖርዎታል። ስለነዚህ መብቶችና ጥቅሞች ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት በዚህ መመሪያ ውስጥ ያለውን ገጽ 47 ይመልከቱ። የዓለም አቀፉ ይግባኝ ፍ/ቤት ከዓለምአቀፍ ጥበቃ ቢሮ (IPO) ውሳኔ ጋር ከተስማማ እና ጥገኝነት የማያስፈልግዎ ሆኖ ካገኘው፣ ማህበራዊ ባለሙያዎ እና / ወይም ጠበቃ ቀጥሎ ምን ማድረግ እንዳለብዎት ያነጋግርዎታል።



# 5.

# የዓለም አቀፍ ፕበቃ ቢሮ (IPO) ሂደት

# የአሰራር ሂደቱን በእያንዳንዱ ደረጃ ላይ ጠለቅ ብለን እንመርምር፡-

## አጭር ቃለ መጠይቅ

የእርስዎ ማህበራዊ ባለሙያ ጥገኝነትን ለማግኘትማመልከቻ ሲያቀርቡ ወደሚችሉበት ደብሊን ወደሚገኘው የዓለምአቀፍ ጥበቃ ቢሮ(IPO) ከእርስዎ ጋር አብረው ይሄዳሉ። የዓለምአቀፍ ጥበቃ ቢሮ ሠራተኛ ከእርስዎ እና ከማህበራዊ ባለሙያዎ ጋር አጭር ቃለ መጠይቅ ያደርጋል። **በዚህ ቃለ መጠይቅ ስለ ማንነትዎ ፣ የወላጆችዎ ማንነት ፣ የትውልድ አገርዎ፣ ወደ አየርላንድ የተጓዙበትን መንገድ እንዲሁም ለጥገኝነት ያመለከቱበትን ምክንያት በተመለከተ ጥያቄ ይጠየቃሉ።** እድሜዎ ከ14 ዓመት በላይ ከሆነ ፎቶግራፍዎና የጣት አሻራዎም ይወሰዳል፣ ይህ የዓለምአቀፍ ጥበቃ ቢሮ(IPO) ማንነትዎን እንዲያረጋግጥና በአውሮፓ ህብረት (EU) ውስጥ በሌላ አገር ጥገኝነት ያመለከቱ መሆን አለመሆኑን ለማረጋገጥ ይረዳሉ። ማመልከቻዎን ሲያቀርቡ የዓለምአቀፍ ጥበቃ ቢሮ ካርድ እና ማጣቀሻ ቁጥርም እንዲሁ ይሰጥዎታል ይህንንም በሁሉም ጊዜ ከራስዎ ጋር ማቆየት ይኖርብዎታል።

## መጠይቅ

የዓለምአቀፍ ጥበቃ ቢሮ (IPO) መጠይቁን እንዲሞሉ እና ወደ ዓለምአቀፍ ጥበቃ ቢሮ ጽ/ቤት መልሰው እንዲልኩ ይጠይቅዎታል። ይህ መጠይቅ ስለ እርስዎ እና የጥገኝነት ጥያቄዎ ተጨማሪ **ዝርዝር ጥያቄ ይጠይቃል።** የእርስዎ ማህበራዊ ባለሙያ እና ጠበቃ መጠይቁን እንዴት እንደሚሞሉ የተወሰነ ምክር ይሰጡዎታል። የተጠናቀቀው መጠይቅ የዓለምአቀፍ ጥበቃ ቢሮ ሠራተኛ ወደ ሀገርዎ ለመመለስ የሚፈሩባቸውን ምክንያቶች እንዲረዱ ያግዛል። ለረዥሙ ቃለ መጠይቅዎ እንዲዘጋጁም ይረዳቸዋል።



## ረጅም ቃለ መጠይቅ

የዓለም አቀፍ ጥበቃ ቢሮ ማህበራዊ ባለሙያዎ ለረዥም ጊዜ ቃለ መጠይቅ ቀጠሮ የተያዘበትን ቀን የሚያሳውቅ ደብዳቤ ይልካል። በአየርላንድ ውስጥ ጥገኝነት የሚያስፈልግዎ መሆኑን ለመመርመር ዋናኛው ረዥሙ ቃለ-መጠይቅዎ ነው። አንዳንድ ጊዜ የእርስዎ **ግላዊ ወይም ዋና ቃለ መጠይቅ ተብሎ ይጠራል** ። ለዚህ የቃለ መጠይቅ እንዲዘጋጁ የህግ ጠበቃዎ እና ማህበራዊ ባለሙያዎ ያግዙዎታል። የዓለም አቀፍ ጥበቃ ቢሮ (IPO) ሠራተኛ የእርስዎን መጠይቅ ጨምሮ ከማመልከቻዎ ጋር የተያያዘ ሁሉንም ወረቀቶችዎን ያነባል። እሱ ወይም እሷ ከቃለ መጠይቁ በፊት ስለ ትውልድ አገርዎ መረጃ ያጣራሉ፤ ይህ መረጃ **የመጡበት አገር** ወይም COI መረጃ ይባላል።

### ለቃለ-መጠይቅዎ አስተርጓሚ እንዲኖር ይፈልጋሉ ወይም አስተርጓሚ ቢኖርይመርጣሉ?

ከቃለ መጠይቁ ቀን በፊት ለማህበራዊ ባለሙያዎ እና / ወይም ጠበቃዎ ማሳወቅዎን ያስታውሱ።

### በወንድ ወይስ በሴት የዓለም አቀፍ ጥበቃ ቢሮ IPO ሠራተኛ ቃለ መጠይቅ ቢደረግልዎት ነው የበለጠ ምቾት የሚሰማዎት?

ለቃለ መጠይቁ ወንድ ወይም ሴት አስተርጓሚ እንዲኖርዎት ሊፈልጉ ይችላሉ። ከቃለ መጠይቁ ቀን በፊት ለማህበራዊ ባለሙያዎ እና / ወይም ጠበቃዎ ማሳወቅዎን ያስታውሱ። ይህንን ተከትሎ የዓለም አቀፍ ጥበቃ ቢሮዉ (IPO) አስተርጓሚው እና ቃለ መጠይቅ አድራጊው እርስዎ በጠየቁት መሰረት ወንድ ወይም ሴት መሆናቸውን የሚወስን ይሆናል።

"የእንግሊዘኛ ቋንቋን በደንብ መናገር ስለማልችል አስተርጓሚ እፈልጋለሁ።

እንዲሁም ለመናገር አስቸጋሪ የሚሆኑብኝ የታሪኬ አንዳንድ ክፍሎች አሉ፣ አስቴርን የሴት ቃለ መጠይቅ እና አስተርጓሚ እንዲኖረኝ እጠይቃታለሁ ብዬ አስባለሁ። ይህም በቃለ መጠይቁ ላይ የበለጠ ምቾት እንዲሰማኝ ያደርጋል።"



ይህ ቃለ-መጠይቅ ብዙ ጊዜ 2 ወይም 3 ሰዓታት የሚፈጅ ቢሆንም፣ በዚህ ጊዜ ውስጥ መደበኛ እረፍት እንዲወስዱ ይፈቀዳል። **ዕረፍት ካስፈለገዎ ለዓለም አቀፍ ጥበቃ ቢሮ(IPO) ሠራተኛ መንገር የሚችሉ ሲሆን እሱ ወይም እሷ የሚያስፈልግዎትን ጊዜ ይሰጥዎታል።** በዚህ ቃለ መጠይቅ ሐቀኛና እውነተኛ መሆን እንዲሁም በሚያስታውሱት መጠን ብዙ ዝርዝሮችን መስጠት አስፈላጊ ነው። የዓለም አቀፍ ጥበቃ ቢሮ(IPO) ሠራተኛሠራተኛ የእርስዎን ታሪክ ለመስማት ይፈልጋል፣ እንዲሁም እርስዎ እንዲናገሩ ለማገዝ ጥያቄዎችን ይጠይቃል። ይህ በአየርላንድ ውስጥ ጥገኝነት እንዲያገኙ የሚያስገድዱዎትን ምክንያቶች በሙሉ ለእሱ ወይም ለእሷ ለመንገር የእርስዎ ዋና አጋጣሚ ነው። **በአገርዎ ውስጥ ያጋጠሙዎትን መጥፎ አጋጣሚዎች ለዓለም አቀፍ ጥበቃ ቢሮ ሠራተኛ ለመናገር አይፍሩ።**(IPO) በቃለ መጠይቅ ውስጥ የሚያወሩት ነገር **በአገርዎ ውስጥ ላለ ለማናቸውም ሰው ሊነገር አይችልም ።**

**የዓለም አቀፍ ጥበቃ ቢሮ** (IPO) **ሠራተኛሠራተኛው ከሚጠይቁዎት ማንኛውንም ጥያቄ መሀከል ያልገባዎ ካለ ይንገሩት እና ጥያቄውን እንዲደግም ወይም እንደገና እንዲያብራራ ይጠይቁ።** ቃለመጠይቁ በጽሁፍ ተመዝግቦ ከ ዓለም አቀፍ ጥበቃ ቢሮ (IPO) ሠራተኛውሠራተኛው ዘንድ ይቀመጣል። እሱ ወይም እርሷ በየመሃሉ ቃለ መጠይቁን ገታ አድርገው መዝገቡ ላይየተጻፈውን ለእርስዎ መልሰው ያነባሉ። ሠራተኛው ትክክለኛው መሆኑን ለማረጋገጥ ይጠይቅዎታል።

## አስፈላጊ

የጽሑፍ ዘገባ ለእርስዎ በሚነበብበት ጊዜ በጥንቃቄ ማዳመጥ በጣም አስፈላጊ ነው ሁሉም ነገር እርስዎ እንደተናገሩት በትክክል ተመዝግቧል? በጽሑፍ የቀረበው መረጃ ሁሉ ትክክል ነውን? የታለፉ አንዳንድ ጠቃሚ መረጃዎች አሉ? ለዓለም አቀፍ ጥበቃ ቢሮ (IPO) ሠራተኛ ትክክል መሆኑን ወይም አለመሆኑን ይንገሩት። እሱ ወይም እርሷ በጽሁፍ ውስጥ ያሉ ማናቸውንም ስህተቶች ያስተካክላሉ። በተጨማሪም ከዚህ በፊት የረሱትን ነጥብ ያስታውሱ ይሆናል። ይህን መረጃ ለዓለም አቀፍ ጥበቃ ቢሮ (IPO) ሠራተኛ የሚሰጡበት ጊዜ አሁን ነው፤ ምክንያቱም እሱ ወይም እሷ የጥገኝነት ማመልከቻዎ ላይ በሚወስኑበት ጊዜ በጣም ጠቃሚ ሊሆን ይችላል። የተመዘገበው መረጃ ትክክል እንደሆነ ከተሰማዎ እርስዎ መፈረም ይችላሉ። የእርስዎ ፊርማ ማለት በዚህ ገጽ ላይ የተፃፉት ሁሉም ነገሮች ትክክልና እውነት ናቸው ማለት ነው።


# በዓለም አቀፍ ጥበቃ ቢሮ (IPO) ያለው የቃለ መጠይቅ ክፍል ይህን የሚመስል ነው።

በቃለ-መጠይቁ ወቅት፣ እያንዳንዱ ግለሰብ የተለየ ሚና አለው እናም እያንዳንዳቸው በተለየ ቦታ ላይ ይቀመጣሉ። በቃለ መጠይቅ ክፍል ውስጥ ያሉ ሰዎች የተለያዩ ሚናዎችን በቅርበት እንመልከታቸው።

ማህበራዊ ባለሙያ




አስተርጓሚ
የዓለም አቀፍ ጥበቃ ቢሮ (IPO) ሠራተኛ



### የዓለም አቀፍ ጥበቃ ቢሮ (IPO) ሠራተኛ

የዓለም አቀፍ ጥበቃ ቢሮ ሠራተኛ ለቃለ መጠይቁ ኃላፊነት አለበት። እሱ ወይም እሷ ስለ የጥገኝነት ማመልከቻዎ ጥያቄዎች ይጠይቁዎታል እና እርስዎ የሚሉትን ሁሉ በጥንቃቄ ያዳምጣሉ። እሱ ወይም እሷ ይህን መረጃ በኮምፒተር ወይም በፅሁፍ ይመዘግባሉ። ይህ **የቃለ መጠይቅ መዝገብ** በመባል ይታወቃል።



### ማህበራዊ ባለሙያ

የእርስዎ ማህበራዊ ባለሙያ ከእርስዎ ጋር በቃለ መጠይቅ ስፍራ ይገኛል። እሱ ወይም እሷ ለእርስዎ ድጋፍ ቢሆኑም ግን እርስዎ በራስዎ ቃላት ለጥያቄዎችዎ ምላሽ እንዲሰጡ ይጠበቅብዎታል። በቃለ መጠይቁ መጨረሻ የዓለም አቀፍ ጥበቃ ቢሮ ሠራተኛ ማህበራዊ ባለሙያውን ስብሰባው ከመዘጋቱ በፊት ሌላ ተጨማሪ ነገር ካለ እንዲጨምሩ መጠየቅ ይችላል። ጠበቃዎ አስፈላጊ ሆኖ ከተሰማው ወደ ቃለ-መጠይቅ ሊሄድ ይችላል።





አስተርጓሚ

በቃለ-መጠይቁ ወቅት እርስዎን ለማገዝ አስተርጓሚም ሊኖርዎ ይችላል። አስተርጓሚው እርስዎ፣ የዓለም አቀፍ ጥበቃ ቢሮ ሠራተኛ እና ሌሎች በቃለ-መጠይቁ ክፍል ውስጥ ያላችሁ ሰዎች እርስበርስ እንድትነጋገሩ ይረዳል። ተርጓሚዎች እንግሊዝኛን እና እርስዎ የሚናገሩትን ቋንቋ ይናገራሉ። አስተርጓሚው የዓለም አቀፍ ጥበቃ ቢሮ ሠራተኛን ጥያቄዎች ወደ እርስዎ ቋንቋ እና ወደ እንግሊዝኛ ይተረጉማቸዋል። እርስዎ እና በዚያ የሚገኙ ሰዎች በግልጽ እንድትግባቡ በማገዝ ረገድ ቁልፍ ሚና ይጫወታል/ለች እናም በመጀመሪያ በቋንቋ መግባባት መቻላችሁን ማረጋገጥ አስፈላጊ ነው።

ያስታውሱ አስተርጓሚዎች የራሳቸውን አስተያየት እንዲሰጡ አይፈቀድላቸውም ወይም የሚናገሩትን እንዲቀይሩ አይፈቀድላቸውም። አስተርጓሚው ለመግባባት ብቻ የሚረዳ ሲሆን በሚሰጠው ውሳኔ ውስጥ ምንም ሚና የለውም።

አስተርጓሚዎች ስለእርስዎ ለሌሎች ሰዎች እንዲናገሩ አይፈቀድላቸውም። ቃለ መጠይቁን በምስጢር መያዝ አለባቸው ስለዚህ ወደ ትውልድ ሀገርዎ ለመመለስ ለምን እንደሚፈሩ በእነሱ ፊት ለመናገር አይፍሩ።

## አስፈላጊ

አስተርጓሚው የሚለውን በደንብ የማይረዱ ከሆነ የዓለም አቀፍ ጥበቃ ቢሮ ሠራተኛወይም የእርስዎ ማህበራዊ ባለሙያ ወዲያውኑ ማሳወቅ አለብዎ። ይህ<u>በእርስዎ</u> የጥገኝነት ማመልከቻ ላይ አሉታዊ ተጽእኖ የሚያስከትል ደለምአይደለም ይልቁንም የዓለም አቀፍ ጥበቃ ቢሮ ቃለ-ምልልስ ወደ ሌላ ቀን ይለወጥና እርስዎም በሚረዱት አስተርጓሚ አማካኝነት ይከናወናል ማለት ነው።

ከቃለ መጠይቅዎ በኋላ የዓለም አቀፍ ጥበቃ ቢሮ ሠራተኛ የጥገኝነት ማመልከቻዎን ይበልጥ ይመረምራል። ይህን ለማድረግ፣ እሱ ወይም እሷ የሚከተሉትን ነገሮች ይመረምራሉ፡-

- **ባለፉት ጊዜያት ለእርስዎ ወይም ሌሎች በእርስዎ ቅርብ በሆኑ ሰዎች ላይ ስለተከሰተ ነገር የሰጡትን መረጃ**
- **.በአገርዎ አጠቃላይ ሁኔታ፣ የትውልድ ሀገር መረጃ ምን እንደሚል ጨምሮ**
- **ወደ ትውልድ ሀገርዎ ከተመለሱ አደጋ ወይም ስቃይ ሊደርስብዎት የሚችልበት ዕድል ስለመኖሩ**

አንዳንድ ጊዜ መረጃን ለማብራራት ተጨማሪ መረጃ ቢያስፈልግ ወይም የዓለም አቀፍ ጥበቃ ቢሮ (IPO) ሠራተኛ ተጨማሪ ጥያቄ ካለ፣ሰዎች ለሁለተኛ ቃለ መጠይቅ ወደ ዓለም አቀፍ ጥበቃ ቢሮ (IPO) ይመለሳሉ።



**ለዓለም አቀፍ የጥበቃ አገልግሎት አመልካቾች የሆኑ ከወላጆቻቸው የተለዩ ልጆች እና ወጣቶች የጥገኝነት አሠራር ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት ከዓለም አቀፍ የጥበቃ ቢሮ የብቸኛ ለአቅመ-አዳም ያልደረሱ / ከቤተሰቦቻቸው የተለዩ ሕፃናት መረጃ መጽሔት ማንበብ ይችላሉ።**

## "ከዓለም አቀፍ ጥበቃ ቢሮ (IPO) ሠራተኛ ጋር ረዥሙን ቃለ ምልልስ ካደረጉልኝ ከጥቂት ሳምንታት በኋላ እንደገና ቃለ መጠይቅ ለማድረግ አነጋገሩኝ።

እኔ ተጨንቄ ነበር ነገር ግን ማህበራዊ ባለሙያ የነበረችው አስቴር ሌላ ቃለመጠይቅ ማድረጉ ጥሩ መሆኑን አረጋገጠችልኝ። የዓለም አቀፍ ጥበቃ ቢሮ(IPO) ሠራተኛ በጣም ተግባቢ እና የነበረ ሲሆን ስለ ማመልከቻዬ አንዳንድ መረጃ ለመፈተሽ ፈልገው ነበር።"



# 6.

# የዓለም አቀፍ ፕበቃ ቢሮ (IPO) ውሳኔ

# ከቃለ መጠይቅዎ ጥቂት ጊዜ በኋላ ማህበራዊ ባለሙያዎ ከዓለም አቀፍ ጥበቃ ቢሮ (IPO) ውሳኔ ያገኛል።

ይህ ውሳኔ ምክረ ሃሳብን የያዘ ሲሆን የስደተኛነት ሁኔታ ወይም የንዑስ ጥበቃ ሲሰጥዎት ከፍትህ እና እኩልነት ሚኒስትር ሌላ ዲክላሬሽን የሚባል ህጋዊ ደብዳቤ ይላክልዎታል። እባክዎ ይታገሱ በጥገኝነት ማመልከቻዎ ላይ የመጨረሻ ውሳኔ ከማግኘትዎ በፊት አንዳንድ ጊዜ ትንሽ ጊዜ ሊቆዩ ይችላሉ።

ሊያገኟቸው የሚችሏቸው የተለያዩ ውሳኔዎች አሉ:

- የስደተኝነት ሁኔታ እርዳታ (አዎንታዊ ውሳኔ)።
- የንዑስ ጥበቃ እርዳታ። የንዑስ ጥበቃ እርዳታ ከተፈቀደሎት የስደተኛነት ሁኔታን እንዲሰጥዎ ውሳኔውን አሁንም ይግባኝ መጠየቅ ይችላሉ.።
- የስደተኝነት ሁኔታም ንም ሆነ ንዑስ ጥበቃም ከተከለከሉ ሚኒስትሩ "የመቆየት ፈቃድ" ይሰጥዎት ወይስ አይሰጥዎት በሚለው ላይ ይወስናል። ለመቆየት ፈቃድ ከተሰጥዎት ግን የስደተኛ ፍቃድ ደረጃ ወይም የንዑስ ጥበቃ እንዲሰጥዎ አሁንም ይግባኝ ማለት ይችላሉ።

ውሳኔ ከዓለም አቀፍ ጥበቃ ቢሮ (IPO) ከተሰጠው በኋላ የህግ ጠበቃዎ እና ማህበራዊ ባለሙያዎ ስለ አማራጮችዎ ያነጋግርዎታል።

# 7.


# የዓለም አቀፍ ጥበቃ ይግባኞች ጉባዔ

# በዓለም አቀፍ ጥበቃ ቢሮ የጥገኝነት እውቅና ጥያቄ ደረጃ ወይም የንዑስ ጥበቃ ካልተሰጠዎ፣ እነዚህን ውሳኔዎች ወደ የዓለም አቀፉ ጥበቃ ይግባኞች ጉባዩ IPAT ይግባኝ ማለት ይችላሉ።

በዓለም አቀፍ ጥበቃ ቢሮ (IPO) የንዑስ ጥበቃ ከተፈቀደልዎት ነገር ግን የስደተኛነት ፈቃድ ሊሰጠኝ ይገባል ብለው የሚያስቡ ከሆነ ይህን ውሳኔ ይግባኝ ማለት ይችላሉ። የእርስዎ ጠበቃ እና ማህበራዊ ባለሙያ ለእርስዎ ጉዳይ ካመለከቱ እነዚህን አማራጮች ለእርስዎ ይነግሩዎታል።

የዓለም አቀፍ ጥበቃ ቢሮ (IPO) ውሳኔን ይግባኝ ማለት ምን ማለት ነው? **ይህ ማለት የዓለም አቀፍ ጥበቃ ቢሮ ውሳኔ ስህተት መሆኑን እና በአየርላንድ የጥገኝነት ማመልከቻ እንደሚያስፈልግዎ ያምናሉ ማለት ነው።** የዓለም አቀፉ ጥበቃ ይግባኞች ጉባዔ ገለልተኛ የሆነ ችሎት(IPAT)፣ ሲሆን ውሳኔው ትክክል መሆኑን ወይም አለመሆኑን ለማረጋገጥ ውሳኔውን ይገመግማል።

የእርስዎ የህግ ባለሙያ በዓለም አቀፍ ጥበቃ ቢሮ ውሳኔ ላይ ይግባኝ በሚሰጥበት ጊዜ ለ**ለ IPAT አቤቱታዉን የሚሰማበትን ቀን ሳዉቃል** ። በዚህ ጊዜ እርስዎ፣ የእርስዎ ማህበራዊ ባለሙያ፣ ጠበቃዎ እና የዓለም አቀፍ ጥበቃ ቢሮ ሠራተኛ (IPO) ከ IPAT አባል ጋር ስብሰባ ታደርጋላችሁ። የህግ ባለሙያዎ የዓለም አቀፍ ጥበቃ ቢሮ (IPO)ውሳኔ የተሳሳተ ነው ያለበትን ምክንያትያብራራል። በይግባኝ መስማት ሂደቱ ወቅት የጉባዔው አባል አንዳንድ ጥያቄዎች ሊጠይቅዎት ይችላል።



"ይግባኝ በሚሰማበት ጊዜ ጉባዔየጉባዔው አባል የዓለም አቀፍ ጥበቃ ቢሮ ሠራተኛ ከጠየቁኝ ጋር ተመሳሳይ ጥያቄዎችን ጠየቁኝ። የማህበራዊ ባለሙያዬ እና ጠበቃዬ አስቀድመው በደንብ አዘጋጅተውኛል፤ ስለዚህ ምን እንደሚጠብቀኝ አውቅ ነበር። በአሰራር ሂደቱ መጀመሪያ ላይ ጉባዔየጉባዔው አባል የሆነ ሰው ሂደቱን ለመረዳት እንድንችል ቀላል በሆነ መንገድ ገለጻ አደረጉልን።"

# የዓለም አቀፍ ጥበቃ የይግባኞች ጉባዔ የይግባኝ መስሚያ ክፍል ምን እንደሚመስል እንመልከት።

በይግባኙ ጊዜ እያንዳንዱ ግለሰብ የተለየ ሚና አለው፣ እናም እያንዳንዱ ሰው በተወሰነ ቦታ ላይ ይቀመጣል። ሰዎች በይግባኝመስሚያ ክፍል ውስጥ ያላቸውን የተለያዩ ሚናዎች እንመልከታቸው።




የ IPAT አባል
IPOን ወክሎ
የሚቀርበው ሠራተኛ




የጉባዔ አባል ችሎቱን ይመራል። እሱ ወይም እሷ ስለ የጥገኝነት ማመልከቻዎ ጥያቄዎች ይጠይቁዎታል እና እርስዎ የሚሉትን ሁሉ በጥንቃቄ ያዳምጣሉ። እሱ ወይም እሷም በችሎት ጊዜ አንዳንድ ማስታወሻዎችን ሊወስዱ ይችላሉ።





በአቤቱታ ወቅት እርስዎን የሚረዳ አስተርጓሚ ሊኖርዎ ይችላል። አስተርጓሚው እርስዎ፣ የጉባዔው አባል እና ሌሎች በይግባኝ መስሚያው ክፍል ውስጥ ያላችሁ ሰዎች እርስበርስ እንድትነጋገሩ ይረዳል። ልክ እንደ የዓለም አቀፉ ጥበቃ ቢሮ ሁሉ የአስተርጓሚው ሚና እርስዎ የተናገሯቸውን በሙሉ፣ ለጉባዔ አባል እና ለሌሎች ችሎት ውስጥ ላሉ ሰዎች መተርጎም ነው። አስተርጓሚውን በትክክል መረዳትዎን ያረጋግጡ። አስተርጓሚው የሚለውን በደንብ የማይረዱ ከሆነ ለጉባዔው አባል ወይም እና/ወይም ለእርስዎ ማህበራዊ ባለሙያ ወዲያውኑ ማሳወቅ አለብዎ። ያስታውሱ ይህ በጥገኝነት ማመልከቻዎ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ አይኖረውም እና እርስዎ በሚረዱት አስተርጓሚ የIPAT የፍርድ ችሎቱ ወደ ሌላ ቀን ከነአስተርጓሚዉ ይቀየራል ማለት ነው።



## ማህበራዊ ባለሙያ እና ጠበቃ

የእርስዎ ማህበራዊ ባለሙያ እና ጠበቃ ከእርስዎ ጋር ወደ ይግባኝ አቤቱታ ስፍራ ይሄዳሉ። እነሱ ለእርስዎ ድጋፍ ለመስጠት ነዉ የሚገኙት ፣ ነገር ግን በራስዎ ቃላት ጥያቄዎችን እንዲመልሱ ይጠየቃሉ። አንዳንድ ጊዜ የጉባዔ አባል ከጥገኝነት ማመልከቻዎ ጋር በተያያዙ ጉዳዮች ላይ ጠበቃዎ እና የማህበራዊ ባለሙያዎ እንዲናገሩ ይጠይቃል። ጠበቃዎ ለምን የጥገኝነት ጥያቄ እንደሚፈልጉ ሕጋዊ መከራከሪያዎችን ያቀርባል።



## IPOን ወክሎ የሚቀርበው ሠራተኛ

ከዓለም አቀፉ ጥበቃ ቢሮ አንድ ሠራተኛም በችሎቱ ላይ ይገኛል። በ IPAT የይግባኝ መስማት ሂደት ላይ፣ ይህ ሠራተኛ ስለ የዓለም አቀፉ ጥበቃ ቢሮ (IPO) ውሳኔ በጉባዔ አባል ሊጠየቅ ይችላል።

## ምስክር

አንዳንድ ጊዜ ምስክሮች በ IPAT ይግባኝ መስማት ሂደት ላይ ሊሳተፉ ይችላሉ። አንድ ምስክር የእርስዎን የጥገኝነት ማመልከቻ በተመለከተ ለጉባዔ አባል ጠቃሚ መረጃ ለእርስዎ እና / ወይም ለቤተሰብዎ አንድ ነገር እንደተከሰተ ይመሰክሩሎታል። ለጥገኝነት ማመልከቻዎ የሚመለከት ከሆነ ጠበቃዎት ስለሚያውቅ ስለዚህ ጉዳይ ያነጋግርዎታል።

የጉባዔ አባል የዓለም አቀፉ ጥበቃ ቢሮ(IPO) የተሳሳተ ውሳኔ እንዳደረገ አድርጎ ካሰበ ፣ አዲስ ውሳኔ ይወስናሉ። ከዚያም የፍትህ እና እኩልነት ሚኒስተር የጉባዔ አባል በሚወስነው መሰረት የስደተኞችን ሁኔታ ወይም የንዑስ ጥበቃን በተመለከተ መግለጫ ይሰጥዎታል።



**የIPAT ከህጻናት እና ከወጣቶች ይግባኝ የሚሰማበት ልዩ መመሪያዎች አሉት።**
**ለተጨማሪ መረጃ** የዓለምአቀፍ ጥበቃ ችሎት መመሪያዎችን ይመልከቱ ። ቁ. 2017/5 ከህጻን አመልካቾች የሚቀርብ ይግባኞች።



## ወደ IPAT ያቀረቡት ይግባኝ ካልተሳካልዎት እና ቀደም ሲል በዓለም አቀፉ ጥበቃ ቢሮ እንዲቆዩ ከዚህ በፊት የንዑስ ጥበቃ ወይም ፈቃድ ካልተሰጠዎትም ፣ ለፍትህ እና እኩልነት ሚኒስቴር አዳዲስ መረጃዎችን ለማቅረብ 5 ቀናት ይኖርዎታል።

ይህ መረጃ ለምን የመቆየት ፍቃድ ሊሰጥዎ እንደሚገባ ያብራራል። እርስዎ፣ ማህበራዊ ባለሙያዎ እናወይም ጠበቃዎ ይህንን መረጃ በተቻለ ፍጥነትማቅረብ አስፈላጊ ነው። ከዚያም የፍትህ እና እኩልነት ሚኒስትሩ የመጀመሪያውን ውሳኔ ከልሰው ለምን የመቆያ ፈቃድ እንዳልተሰጠዎ ያያሉ። ለመቆየት ያልተፈቀዱ ከሆነ የህግ ባለሙያ እና ማህበራዊ ባለሙያ ለእርስዎ ስለሚገኙ አማራጮች በሙሉ ይነጋገራሉ፣ በሀገርዎ ከቤተሰብዎ ጋር እንደገና እንዲገናኙ ማድረግንም ያካትታል.።



# 8.

# ሌላ መረጃ

# የዕድሜ ግምገማ ሂደት ምንድን ነው?

አንዳንድ ጊዜ የዓለም አቀፍ ጥበቃ ቢሮ ሠራተኛ ወይም የተስላ ማህበራዊ ባለሙያ ስለእድሜዎ ጥርጣሬ ካደረባቸው የዕድሜ ግምገማ እንዲካሄድ ይደረጋሉ። ይህ ከዓለም አቀፍ ጥበቃ ቢሮ እና/ ወይም ተስላ ጋር የተለየ ቃለ ምልልስ ሊያደርግ ይችላል። የማንነት መታወቂያ ወረቀት፣ የልደት የምስክር ወረቀት ወይም ዕድሜዎን የሚያሳዩ ሌሎች መረጃዎች ካለዎት ከማህበረሰባዊ ሰራተኛዎ እና ከዓለም አቀፍ ጥበቃ ቢሮ ሠራተኛ ጋር ይጋሩ። IPO ለ 18 ዓመት ዕድሜዎ ለእርስዎ የጥገኝነት ጥያቄ አላማ ከወሰኑ በሂደቱ የጥገኝነት አሰጣጥ ሂደት ውስጥ እንደ ትልቅ ሰው ሆነው ይመረመራሉ። ይህም ማለት አሁን ካለው መኖሪያዎ እንዲለቁ እና ወደ ተለየ የመኖሪያ ቦታ መንቀሳቀስ ያለብዎት ሲሆን ይህም የቀጥታ የእቅድ አቅርቦት ማዕከል በመባል ይታወቃል።

# የአውሮፓ ሕብረት የደብሊን ደንብ ምንድን ነው?

የአውሮፓ ሕብረት (አሕ)የደብሊን ደንብ በአውሮፓ ህብረት ውስጥ የተደረጉ የሀገሮች መካከል ስምምነት ማለት ነው። በአውሮፓ ህብረት ውስጥ የትኛው ሀገር የእርስዎን የጥገኝነት ማመልከቻ መመርመር እንዳለበት ለመወሰን የሚረዱ ደንቦችን ያመላክታል። ይህ የዲብሊን ሕግ በመባል ይታወቃል ምክንያቱም ስምምነቱ በዳብሊን ውስጥ ስለተፈረመ።

እናትህ ፣ አባትህ ፣ እህትህ ፣ ወንድምህ ፣ አክስት ወይም አጎትህ በአውሮፓ ውስጥ በሌላ ሀገር ይኖራሉ? እነርሱን መቀላቀል ይፈልጋሉ? እባክዎን በተቻለ ፍጥነት በሌሎች የአውሮፓ ህብረት ሀገሮች ስላሉት የቤተሰብዎ አባላት ለጠበቃና ማህበራዊ ባለሙያ ይንገሩ። የዓለም አቀፍ ጥበቃ ቢሮ ጽህፈት ቤትየጥገኝነት ማመልከቻዎን ሊመረምር ይችላል ፣ ስለዚህ ሄደው ቤተሰቦችዎን እዚህ ውስጥ ይቀላቀሉ።

የዲብሊን ህግ በእርስዎ ጉዳይ ላይ ተግባራዊ ከሆነ ጠበቃዎ የበለጠ መረጃ ሊሰጥዎት ይችላል።

# ቅድሚያ መስጠት ማለት ምንድን ነው?

የእርስዎ ማህበራዊ ባለሙያ ወይም ጠበቃ ስለ ማመልከቻዎ ቅድሚያ መስጠትን ሲናገሩ መስማት ይችሉ ይሆናል። ይህ ማለት፣ ማመልከቻዎ በተወሰኑ ምድቦች ውስጥ ከተመደበ "ቅድሚያ የሚሰጠው" ሊሆን ይችላል እና ቃለ መጠይቅዎ በተቻለ ፍጥነት ይደራጃል። ማመልከቻዎች ቅድሚያ የሚሰጣቸው ምክንያቶች የሚከተሉትን ያጠቃልላሉ: እርስዎ ያለ ምንም ወላጅ ከሆኑ፣ ከባድ የጤና ችግር ካለብዎት፣ ወይም ከሚከተሉት አገሮች ውስጥ ከአንዱ ከሆኑ: ሶሪያ፣ ኤርትራ፣ ኢራቅ፣ አፍጋኒስታን፣ ኢራን፣ ሊቢያ ወይም ሶማሊያ።

# የጥገኝነት ማመልከቻዬ እየታየ ባለበት ጊዜ መስራት እችላለሁን?

የጥገኝነት ማመልከቻዎን ባስገቡ በ9 ወራት ጊዜ ውስጥ ከዓለም አቀፍ ጥበቃ ቢሮ ጽ / ቤት ውሳኔ ካላገኙ፣ እርስዎም ልክ እንደ የአየርላንድ ወጣት ሕዝብ በተመሳሳይ መልኩ ለመስራት ፈቃድ ይኖርዎታል። በአየርላንድ ውስጥ ወጣቶችን ለመቅጠር አንዳንድ ሕጎች ያሉ ሲሆን ለምሳሌ ከ 16 ዓመት በታች የሆኑ ልጆች በቋሚነት የሙሉ ሰዓት ሥራ ሊሰሩ አይችሉም ነገር ግን በበጋ ዕረፍት ወቅት አንዳንድ ስራዎችን ሊያከናውኑ ይችላሉ። የማኅበራዊ ባለሙያው የመሥራት መብትዎን በተመለከተ ተጨማሪ መረጃ ያቀርብልዎታል።



**ስለ አውሮፓ ህብረት የዲብሊን ደንብ አሠራር** በዓለም አቀፍ ጥበቃ ቢሮ ዓለም አቀፍ ጥበቃ የሚጠይቁ ሕጻናት የመረጃ መጽሔት ዉስጥ በዳብሊን አሠራር ላይ ተጨማሪ ማንበብ ይችላሉ።

**ስለ የዓለም አቀፍ ጥበቃ ቢሮ ቅድሚያ አሰጣጥ ፖሊሲ ተጨማሪ መረጃ በ** ዓለም አቀፍ ጥበቃ መተግበሪያዎች ቅድሚያ መስጠት በ2015 ድንጋጌ መሠረት የበለጠ ማንበብ ይችላሉ።



# 9. የአርሶዎ መብቶች

# የስደተኛ ፍቃድ ወይም የንዑስ ጥበቃ ደረጃ ከተሰጠዎት መብቶችዎ

የስደተኛ ፍቃድ ወይም የንዑስ ጥበቃ ደረጃ ስምምነት ከተቀበሉ የሚከተሉትን ጨምሮ የተወሰኑ መብቶች አለዎት፡

- በአየርላንድ ውስጥ ቢያንስ ለ 3 ዓመት የመኖር ፈቃድ።
- የሚፈልጉ ከሆነ እንደ አየርላንድ ነዋሪ ወጣት እንዲሰሩ ይፈቀድልዎታል።
- እንደ የአየርላንድ ነዋሪ ወጣት ተመሳሳይ የአንደኛና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት እና ስልጠና መውሰድ ይችላሉ እናም ከሶስት ዓመት ቆይታ በኋላ የሶስተኛ ደረጃ ትምህርት ለመከታተል ብቁ ሊሆኑ ይችላሉ።
- የአየርላንድ ዜጎች ከሚቀበሉት የሕክምና እና የማህበራዊ ዋስትና ጥቅማጥቀሞች ጋር ተመሳሳይ የሆኑ ጥቅማጥቅሞችን መቀበል ይችላሉ።
- እንደ የአየርላንድ ሰዎች ወደ ውጭ አገር መጓዝ ይችላሉ ነገር ግን ወደ ሌላ አገር ለመሄድ ቪዛ ያስፈልግዎት እና / ወይም የጉዞ ሰነድ (እንደ ፓስፖርት) ማመልከት አለብዎት። የስደተኛ ፍቃድ ወይም የንዑስ ጥበቃ ደረጃ ካለዎት ለጉዞ ፓስፖርት ለማመልከት የተለያዩ ሕጎች ስላሉ የማህበራዊ ባለሙያዎን ያነጋግሩ።
- የቅርብ ጊዜ የቤተሰብዎ አባላት ወደ አየርላንድ እንዲመጡ እና ከእርስዎ ጋር እንዲኖሩ ለፍትህ እና እኩልነት ሚኒስቴር ማመልከት ይችላሉ፤ ይህ ቤተሰብን መልሶ ማገናኘት ተብሎ ይጠራል። የስደተኛ ፍቃድ ወይም የንዑስ ጥበቃ ከተደረገ በ 12 ወራት ውስጥ የቤተሰብ መልሶ ማገናኘት ማመልከቻ መደረግ አለበት።
- የስደተኛ ፍቃድ ከያዙ ከ 3 ዓመት በኋላ የአየርላንድ ዜጋ ለመሆን ማመልከት ይችላሉ። የንዑስ ጥበቃ ከተቀበሉ ከ 5 ዓመታት በኋላ የአየርላንድ ዜጋ ለመሆን ማመልከት ይችላሉ።

# ለቤተሰብ መልሶ ማገናኘት ማመልከቻ እንደ የትኛውም የቤተሰብ አባል ማመልከት ይችላሉ?

የስደተኛ ፍቃድ ደረጃ ወይም የንዑስ ጥበቃ ሲደረግልዎት እና ያለ ምንም ወላጅ ከሆኑ እንዲሁም ከ 18 ዓመት በታች ከሆኑ የሚከተሉት የቤተሰብ አባላት በአየርላንድ ውስጥ ከእርስዎ ጋር ለመኖር ማመልከት ይችላሉ።

- **የእርስዎ ወላጆች**

- **ወንድምዎና እህትዎ**
  **ከ 18 ዓመት በታች ያሉ እና ያላገቡ ከሆኑ**

በዓለም አቀፍ የመከላከያ ድንጋጌ መሠረት የፍትህ እና እኩልነት ሚኒስትር እነዚህን ማመልከቻዎች በተወሰኑ ሁኔታዎች ላይ ብቻ ውድቅ ያደርጋሉ። በአጠቃላይ፣ ዕድሜዎ 18 ዓመት ከሆነ እና ቤተሰብዎ እንደገና እንዲቀላቀሉ ማመልከቻ ማቅረብ ይችላሉ ወይም ሌሎች ዘመዶችዎ ወደርስዎ እንዲመጡ ለማመልከት ይችላሉ፣ ነገር ግን ይህ የርስዎ ሁኔታዎች ላይ ይመሰረታል። የእርስዎ ማህበራዊ ባለሙያ ስለዚህ ጉዳይ ያነጋግራል ፣ ቤተሰብዎን መልሶ ለማገናኘት እንዲያመለክቱም ያግዝዎታል።

## አስፈላጊ

በዓለም አቀፉ የሕግ ጥበቃ ድንጋጌ መሰረት በ 12 **ወራት** ውስጥ በስደተኝነት ሁኔታ ወይም በንዑስ ጥበቃ ስርዓት መሰረት ለቤተሰብ መልሶ ማገናኘት ማመልከት አለብዎ። ቤተሰብን መልሶ ማገናኘት ማመልከቻን ለማዘጋጀት ለማህበራዊ ባለሙያ እርዳታ መጠየቅዎን ያስታውሱ።

# ለመቆየት ፈቃድ ከተሰጠት ያለዎት መብቶች

ለመቆየት ፍቃድ ማለት በአንዳንድ ሁኔታዎች በአየርላንድ ለተወሰነ ጊዜ መቆየት ይችላሉ ማለት ነው። የፍትህ እና እኩልነት ሚኒስቴሩ ካመነበት ሁኔታው ካልፈረሰበት በቀር ይህ ፈቃድ በመጨረሻው ክፍለ ጊዜ ሊራዘም ይችላል። አየርላንድ ውስጥ ለ 5 ዓመታት ከኖሩ በኋላ የአየርላንድ ዜጋ ለመሆን ማመልከት ይችላሉ።



"የስደተኛነት ፈቃድ ሲሰጠኝ በጣም ደስተኛ ነበርኩ። አሁን በአየርላንድ ውስጥ ያለኝን የወደፊት እቅድ ማውጣት እችላለሁ።"

ስለመብትዎ ተጨማሪ መረጃ በማንኛውም **የዜጎች መረጃ ጽ / ቤት** ማግኘት ይችላሉ ።

# 10.

# ለአገዛ ሊያገኙ የሚትችሉዋቸው ድርጅቶች ዝርዝር

## ጥገኝነት ለሚፈልጉ ልጆች የተቋቋመው ቡድን ፣ ተስላ - የልጅና የቤተሰብ ድርጅት

በ Sir Patrick Dun's Hospital, Lower Grand Canal Street, ዱብሊን 2 D02 P667 ወይም በስልክ ቁጥር 01 647 7000 በመደወል ማነጋገር ይችላሉ። ለተጨማሪ መረጃ የሚከተለውን ይጎብኙ: **www.tusla.ie/services/alternative-care/separated-children/**

## የሕግ እርዳታ ቦርድ (LAB)፣ የተለያዩ የልጆች ክፍል (የስደተኛ ህጋዊ አገልግሎት)

ጥገኝነት ጠያቂዎችን በጥገኝነት አሰራር ሂደቱ ውስጥ ወጣት ሰዎችን ጨምሮ ህጋዊ ምክር ይሰጣል። ዋና ቢሯቸው በ 48-49 North Brunswick Street, Georges Lane, Smithfield, Dublin 7, D07 PE0C. ላይ የተመሠረተ ነው። ወደ **1800 23 83 43** በመደወል ወይም በኢሜል **smithfieldlawcentre@legalaidboard.ie** ማነጋገር ይችላሉ። ስለ የሕግ እርዳታ ቦርድ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት እና እርዳታ ለማግኘት እንዴት ማመልከት እንደሚችሉ ለማወቅ:- **www.legalaidboard.ie** ላይ ይመልከቱ

## የህፃናት ዕንባ ጠባቂ

የህዝብ ድርጅቶች በሚወስዳቸው እርምጃዎች ላይ በህጻናት እና ወጣቶች የሚነሱ ቅሬታዎችን የሚመለከትጽ / ቤት ነው። አድራሻቸውም:- Millennium House, 52-56 Great Strend Street, Dublin 1. በሚከተሉት አድራሻዎች ሊያገኙዋቸው ይችላሉ:- **1800 202040** ወይም **01 865 6800** ወይም ኢሜይል በመላክ: **oco@oco.ie**.ie ላይ ይመልከቱ ለተጨማሪ መረጃ የሚከተለውን ይጎብኙ:- **www.oco.ie.ie**

## የአየርላንድ ቀይ መስቀል መልሶ ማቋቋም የቤተሰብ አገናኞች አገልግሎት

ከአየርላንድ ውጪ የቤተሰብ አባል ካለዎት ሊረዱዎት ይችላሉ። በሚከተሉት አድራሻዎች ሊያገኙዋቸው ይችላሉ:- **01 642 4600** ወይም **restoringfamilylinks@redcross.ie** ላይ ኢሜይል መላክ.ie ለተጨማሪ መረጃ የሚከተለውን ይጎብኙ: **www.redcross.ie/programmes-and-services-in-ireland/find-missing-family/**

## የልጆች መብቶች ድርጅት

ለህጻናት፣ ለወጣቶች እና ለቤተሰቦቻቸው ወይም ከእነሱ ጋር አብሮ ለሚሠሩ ሰዎች የህግ መረጃን ለማግኘት እርዳታ መስመር አለው። በሚከተሉት አድራሻዎች ሊያገኙዋቸው ይችላሉ:- **01 9020494** ወይም በኢሜይል: **query@childrensrights. ie.** ለህጋዊ የምክር ክሊኒኮች ቀጠሮ ማስያዝም ይቻላል. ለተጨማሪ መረጃ ይጎበኙ፡ **www.childrensrights.ie/content/childrens-access-justice**

## የአየርላንድ ማህበረሰብ የጨካኝነት ወንጀልን የመከላከል ህብረት (ISPCC)

ብሔራዊ የልጆች ጥበቃ የበጎ አድራጎት ድርጅት ነው። ዋናው ቢሮአቸዉ የተመሠረተው በ 29 Lower Baggot Street, Dublin 2. ለሕፃናት የ 24 ሰዓት ብሄራዊ የማዳመጥ አገልግሎት የሚያካሄዱት የህፃን መስመር (ChildLine) ተብሎ ይታወቃል። የግል ነው፣ ሚስጥራዊ እና ፈራጅ አይደለም። በነዚህ ቦታዎች በአየርላንድ ከማንኛውም ቦታ **1800 66 66 66** ጋር በነጻ ሊገኝ ይችላሉ። በተጨማሪም የእነዚህን ድህረ ገፃቸውን በ **www.ispcc.ie** መጎብኘት ይችላሉ። ማለትም

## Barnardos

ለልጆች እና ለቤተሰቦች መብት የሚውል የልጆች ልግስና ነው። ዋናው ቢሮያቸው የተመሠረተው በክርስቶስ ቸርች አደባባይ፣ ዲብሊን 8 ነው። በሚከተሉት አድራሻዎች ሊያገኙዋቸው ይችላሉ:- **1850 222 300** ወይም **01 453 0355** ወይም በኢሜይል፡ **info@barnardos.ie.** በተጨማሪም ድህረ ገጻቸውን እዚህ መጎብኘት ይችላሉ: **www.barnardos.ie**

## ሰዎችን በእንክብካቤ ማጠናከር (EPIC)

በእንክብካቤ ውስጥ የሚገኙ ወጣቶችን መብት የሚደግፍ እንዲሁም በተጨማሪም ከጤና እንክብካቤ እና ከክትትል አገልግሎት ለመውጣት እየተዘጋጁ ካሉ ወጣቶች ጋር ይሰራል.። ሰዎችን በእንክብካቤን ማጠናከር ዱብሊን ቢሮ ጋር በመደወል ማነጋገር ይችላሉ: **01 872 7661**። ዋናው ቢሮያቸው በ 7 Red Cow Lane, Smithfield, ደብሊን 7 ላይ ነው። ለተጨማሪ መረጃ የሚከተለውን ይጎብኙ: **www.epicline.ie**

## SPUNOUT.ie

ወጣቶች፣ ለወጣቶች የተፈጠሩ የአየርላንድ ወጣቶች መረጃ ድረገፅ ነው። ድህረገፁ ትምህርት፣ ሥራ እና ጤናን ጨምሮ የተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮችን ያቀርባል። ለተጨማሪ መረጃ የሚከተለውን ይጎብኙ: **www.spunout.ie**

## BeLonG To የወጣቶች አገልግሎቶች

የአየርላንድ ሌስቢያን ፣ ጌይ፣ ከሁለት ፆታ ትራንስጀንደር እና ኢንተርሴክስ (LGBTI+) ወጣቶችን የሚደግፍ ብሔራዊ ድርጅት ነው። መረጃን እና ያልተፈቀዱ እና ምስጢራዊ ድጋፎችን ያቀርባሉ። ወጣቶችንም ያደራጃሉ። ጽህፈት ቤቱ በ Parliament House, 13 Parliament Street, Dublin 2, D02 P658 ነው። በሚከተሉት አድራሻዎች ሊያገኙዋቸው ይችላሉ:- **01 670 6223** ወይም ኢሜይል በመላክ: **info@belongto.org.** ስለ BeLonG To በሚከተለው ላይ ተጨማሪ መረጃ ማንበብ ይችላሉ: **www.belongto.org**

## የአየርላንድ የስደተኞች ምክር ቤት

ለግለሰቡ መጠይቆች መልስ ለመስጠት እና መረጃን ለመስጠት የሚችሉ የግል ህግ ማእከል እና የመቆያ አገልግሎት አለው። በጥገኝነት አሰራር ሂደት ውስጥ ከጎልማሶች ጋርም ይሰራሉ። በ 37 Killarney Street, Mountjoy, Dublin 1 ላይ የተመሰረቱ እና በ **01 764 5854** በመደወል ሊያነጋግሩ ይችላሉ። የአየርላንድ የስደተኞች ምክር ቤት ድህረ-ገፅ: **www.irishrefugeecouncil.ie**

## /NASC አየርላንድ

በነጻ የእግር ጉዞ አገልግሎት በነፃ ኢሚግሬሽን እና ከጥገኝነት ጋር የተያያዙ ጉዳዮች ላይ የህግ ምክር እና መረጃ ያቀርባል። እነሱ በ 34 Paul Street, Cork, T12 W14H ላይ የተመሠረቱ ናቸው እና በ **021 427 3594** በመደወል ሊገኙ ይችላሉ። ለበለጠ መረጃ የሚከተሉትን ይመልከቱ: **www.nascireland.org**

## ዶራ ሉሚኒ / Doras Luimni

በተለያዩ የኢሚግሬሽን ጉዳዮች ላይ ምክር እና የህግ መረጃን ይሰጣል። እነሱ የተመሠረቱ በማዕከላዊ ሕንፃዎች, 51a O'Connell Street, Limerick. በሚከተሉት አድራሻዎች ሊያገኙዋቸው ይችላሉ:- **061 310 328**. ለተጨማሪ መረጃ የሚከተለውን ይጎብኙ: **www.dorasluimni.org**

## ክሬዲት ኬር / Crosscare

ስለ መኖሪያ ቤት ፣ ማህበራዊ ደህንነት ፣ ትምህርት ፣ የቤተሰብን መልሶ ማገልበት እና ሌላ የኢሚግሬሽን ጉዳዮች መረጃና ምክር ይሰጣል። በ 1 Cathedral Street, Dublin 1 ውስጥ ለስደተኞች የእግር ጉዞ አገልግሎት አላቸው። በሚከተሉት አድራሻዎች ሊያገኙዋቸው ይችላሉ:- **01 873 2844** ወይም በኢሜይል: **crs@crosscare.ie.** ለተጨማሪ መረጃ የሚከተለውን ይጎብኙ: **www.crosscare.ie/refugee-service**

## ጀሱይት የስደተኞች አገልግሎት

አየርላንድ ለጥገኝነት ማመላለስ ፣ የቋንቋ ትምህርት እና የስነ-ልቦና ድጋፍ ለሚፈልጉ ሰዎች እርዳታ ይሰጣል። ዋና ቢሮቸው በ 54-72 Gardiner Street High Dublin 1 D01 TX23 ላይ የተመሰረተ ነው። በሚከተሉት አድራሻዎች ሊያገኙዋቸው ይችላሉ:- **01 814 8644** ወይም በድረገጻቸው ላይ የአድራሻ ቅጽ መሙላት ይችላሉ: **www.jrs.ie/index.php/contact.** ስለ ጀሱይት የስደተኞች አገልግሎት አየርላንድ ተጨማሪ መረጃ በዚህ ላይ ሊመለከቱ ይችላሉ: - **www.jrs.ie**

## SPIRASI

የማሰቃየት ሰለባዎችን ለማገዝ እና የእንግሊዝኛ ፣ የኮምፒዩተር ክህሎቶች እና አርትስን ጨምሮ በተለያዩ ቦታዎች ነጻ ትምህርቶችን ይሰጣል። እነሱ በ 213 North Circular Road, Phibsborough ላይ ተመስርተው በ **01 838 9664** ላይ ሊገኙ ይችላሉ። ለተጨማሪ መረጃ የሚከተለውን ይጎብኙ: **www.spirasi.ie**

# ይህ መመሪያ የተዘጋጀው በተባበሩት መንግስታት የስደተኞች ከፍተኛ ኮሚሽን አየርላንድ ጽ/ቤት ነው።

የተባበሩት መንግስታት የስደተኞች ከፍተኛ ኮሚሽን ከመንግስታት ፣ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች እና ከሌሎች አጋሮች ጋር ስደተኞችን እና አገር አልባ ሰዎች ለመጠበቅ ይሰራል። የእኛን ድህረገጽ እዚህ ላይ መጎብኘት ይችላሉ: - **www.unhcr.org/en-ie**

ቢሮአችንን ለመገናኘት ከፈለጉ ፣ በ **ireduprt@unhcr.org** ኢሜይል ሊልኩልን ይችላሉ፤ ወይም በ **01 631 4510** ላይ ሊደውሉልን ይችላሉ።
ጽ/ቤታችን በ 102 Pembroke Road, Ballsbridge, Dublin 4 ላይ የተመሠረተ ነው።

UNHCR
The UN Refugee Agency

102 Pembroke Road,
Ballsbridge, Dublin 4,

ስልክ +353 (0)1 631 4510
ireduprt@unhcr.org
www.unhcr.org